**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

5ki Diro Kiiro___

Hawaasa, ……. .., 2017M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፭ኛ ዓመት ቁጥር_____

ሀዋሳ ሀምሌ ..፣ ፳፻፲፯ ዓ.ም


**Amado**

**Lallawu Kiiro …/2017**


**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA POOLISE XAPHOOMU BIDDISHSHI TANTANO, BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA MURATE FULINO LALLAWA QOOLA…………………………1**


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር .../፳፻፲፯**


**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ገጽ…………………..፩**


**Lallawu Kiiro …./2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolise Xaphoomu Biddishshi Tantano, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa**

Qoqqowinkera Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma poolisete wolqa bayriidi seeranna bayriidi seeri garinni fultino seerubbanna Itophiyu adhinonna kaajjishino kaaliqete deerri suumumme ayirisatenna ayirisiisate sokkase woyyabbino ikkadimanni fulate tantanosenna loosu harinshose yannite assa hasiissannota ikkitinohura;

Uurrinsha daggate amanamooshshi nooseta,

**አዋጅ ቁጥር …./፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

በክልላችን የሲዳማ ብሄራዊ ክልል መንግስት ፖሊስ ሠራዊት ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን እንዲሁም ህገ መንግስቱን መሠረት አድርጎ የወጡ ህጎችን እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውንና ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የማክበርና የማስከበር ተልዕኮውን በተሻለ ብቃት ለመወጣት አደረጃጀቱን እና አሠራሩን ማዘመን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተቋሙ የህዝብ ተዓማንነት ያለው ሙያዊ ብቃትና

ogimmate ikkadimma, manihiimate qoosso ayirasanna ayirisiisa dandiitannota maladiweelo ikkite xawaadimateninna xa'mamooshshunni loossannota kaajjado poolisete wolqa tantana hasiisinohura;

Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma Bayriidi seeri quwa 48 cinaancho quwa (3) (A) garinni aaninoha lallanboonni

**GAFA MITTE**

**XAPHOOMU WORO**

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa "**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Poolise Xaphoomu Biddishshi Tantano, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro …. /2017**" yine woshshinara dandiinanni.

2. **Qaallate Tiro**

   Qaalu eo wole tiro uyisiissannoha ikka hoogiro konni lallawi giddo:

1) **''Xaphoomu Biddishsha** yaa jefisiisanote lallawi garinni uurrinonna tantanosi kpnni lallawinni gumulantino Qoqqowu poolise qara hajanjanni uurrinshati;

2) **''Xaphoomu biddishshi hajajancho''** yaa poolisete wolqa istratejikete massagaano giddo massagaanchimmate ikkadimanna ikkadu rosichi noosiha ikke Sidaamu Dagoomi Qoqqoqu Mootimma Prezidanetenni moo'tomanno Qoqqowu poolisete wolqa aliidi hajajanchooti;

3) **''Aantano xaphoomu biddishsha''** yaa SDQM Poolise Xaphoomu Biddishshi hunda uurritanno

ሰብዓዊ መብትን ማክበርና ማስከበር የሚችል ገለልተኛ ሆኖ በግልጸኝነትና በተጠያቅነት የሚሰራ ጠንካራ የፖሊስ ሠራዊት ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ **"የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር** ……/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1) ጠቅላይ መምሪያ ማለት በአስፈፃሚ አካላት አዋጅ መሠረት የተቋቋመና አደረጃጀቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የተደነገገ የክልሉ ፖሊስ ዋና ማዘዣ ተቋም ነው፤

2) **"የጠቅላይ መምሪያ አዛዥ"** ማለት ከፖሊስ ሠራዊት ስትራቴጅክ አመራሮች ውስጥ የመሪነት ብቃትና በቂ ልምድ ያለው በስዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት የሚሾም የክልሉ ፖሊስ ሠራዊት የበላይ አዛዥ ነው፤

3) **"ም/ጠቅላይ መምሪያ"** ማለት ሲዳማ ብሄራዊ ክልል መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ስር

qara qara loosu gollati;

4) **‘’Aantano Xaphoomu Biddishshi hajajancho’’** yaa poolisete wolqa istraatejikete massagaano giddo massagaanchimmate ikkadimanna ikkadu rosichi noosiha ikke xaphoomu biddishshi komishiinerichi shiqisheenna Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma Prezidanetichinni moo’tomanno xaphoomu biddishshi hajajanchi aantanonna aantano xaphoomu biddishsha massaganno sooreeyeti;

5) **‘’istratejike massagaano’’** yaa kaa’lanchu komishiinerichinni kayise komishiinerichu suusi geeshsha noo poolisete suusa xaphisannote;

6) **Aliidi massagaano** yaa qara inispekiterete suusunni kayise komaanderete suusi geeshsha noota poolisete suusa xaphisannote;

7) ‘’**Mereerima massagaano**’’ yaa ka’laanchu isnispeekiterichinni kayise inispekiterete suusi geeshsha noo suusa xaphissannote;

8) **‘’Hanafaano massagaano’’** yaa konistaabilete kayise qara saajine geeshsha noota xaphissannote;

9) ‘’**Poolisete wolqa**’’ yaa uurrinshate giddo qaxarante loossanno poolisete miilla gutu su’mishati;

10) **‘’Filantino poolise’’** yaa Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma Poolisete wolqa giddo poolisimatenni owaatate safaraano wonshite dagate giddonni filantinore ikkite poolisete qajeelsha guddinokkire, qixirete sheemata malaatisinokkireti;

*የሚቋቋሙ ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ናቸው፣*

4) *“**“ም/ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ”** ማለት ከፖሊስ ሠራዊት ስትራቴጅክ አመራሮች ውስጥ የመሪነት ብቃትና በቂ ልምድ ያለው በጠቅላይ መምሪያው አዛዥ አቅራቢነት በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት የሚሾም የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ ምክትልና የም/ጠቅላይ መምሪያን የሚመሩ ኃላፍዎች ናቸው፤*

5) *“**ስትራቴጅክ አመራር**” ማለት ከረዳት ኮምሽነር እስከ ኮምሽነር ማዕረግ ድረስ ያሉትን የፖሊስ ማዕረጎች የሚያጠቃልል ነው፤*

6) *“**ከፍተኛ አመራር**” ማለት ከዋና ኢንስፔክተር ማዕረግ እስከ ኮማንደር ማዕረግ ድረስ ያሉትን የፖሊስ ማዕረጎች የሚያጠቃልል ነው፡፡*

7) *“መካከለኛ አመራር” ማለት ከረዳት ኢንስፔክተር ማዕረግ እስከ ኢንስፔክተር ማዕረግ ድረስ ያሉ ማዕረጎችን የሚያጠቃልል ነው፤*

8) *“**ጀማሪ አመራር**” ማለት ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጅን ድረስ ያሉትን የሚያጠቃልል ነው፤*

9) *“**የፖሊስ ሠራዊት**” ማለት በተቋሙ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ የፖሊስ አባላት የወል ስያሜ ነው‹*

10) *“**ምልምል ፖሊስ**” ማለት በሲዳማ ብሄራዊ ክልል ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በፖሊስነት ለማገልገል መስፈርቱን አሟልቶ ከህብረተሰቡ ውስጥ የተመለመለ ሆኖ ፖሊሳዊ ስልጠና ያላጠናቀቀና የቅጥር ውል ያልፈረመ ሰው ነው፤*

11) **‘‘Xintu poolise’’** yaa SDQM Poolisete wolqa giddo poolisimatenni qaxarame owaatanni noo mairege uddirinokki poolisete miilati;

12) **‘‘Poolisete miila’’** yaa xintu poolise qajeelsha woy garimma noose poolisete sayinse rosonna qajeelsha adhi gedensaanni gondooro e’e maasamatenni 7 diro owaatate sheemate eatenni SDQM Poolisete wolqa giddo uurrinshunni qaxarame loosanno pooliseti;

13) **‘’Poolisete Biddishsha’’** yaa zoonnatenna Hawaasi quchumu gashshooti hunda uurrino poolisete wolqa biddishshati;

14) **‘’Poolisete Borro Mine’’** yaa siinu quchumunna woradu gashshooti poolisete wolqa hajanjanni golati;

15) **‘’Siivilete loosaasincho**’’ yaa Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma mootimmate loosaasine seeri woy wolu seeri garinni SDQM poolisete wolqa xaphoomu biddishshi hunda qaxarame loosanno loosaasinchoti;

16) **‘’Gadachoho**’’ yaa aye poolisete miili Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma giddo loosannio aye poolisete owaaneteti;

17) **‘’Baxxitino dandoo**’’ yaa amadino ogimma qixirete woy soorishunni wolu poolisete miilinni woy siviilete loosaasinchinni lekkinsanikki woy dikkote aana afira dandiinanikki baxxitino ogimma woy dandooti;

18) **‘’Horaamiishsha**’’ yaa poolisete miilira woy siivilete loosaasinchira loosu akati garinni

11) ***መሠረታዊ ወታደር*** ማለት በሲዳማ ብሄራዊ ክልል ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በፖሊስነት ተቀጥሮ በማገልገል ላይ ያለ ማዕረግ ያልለበስ የፖሊስ አባል ነው፤

12) ***የፖሊስ አባል*** ማለት መሠረታዊ የፖሊስ ስልጠና ወይም አግባብነት ያለውን የፖሊስ ሳይንስ ትምህርትና ስልጠና ከወሰደ ቦኃላ ቃለ መሀላ ፈጽሞ በመመረቅ 7(ሰባት) ዓመት ለማገልገል ውል በመግባት በሲዳማ ክልል ፖሊስ ሰራዊት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ፖሊስ ነው

13) ***“ፖሊስ መምሪያ“*** ማለት በዞን እና በሀዋሳ ከተማ አስተዳዳር የተቋቋሙ የፖሊስ ሠራዊት መምሪያ ነው፤

14) የፖሊስ ጽ/ቤት ማለት የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አስተዳደር ፖሊስ ሰራዊት ማዘዣ ክፍል ነው፤

15) **“ሲቪል ሰራተኛ”** ማለት በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ህግ ወይም በሌሎች ህጎች መሰረት በሲዳማ ብሄራዊ ክልል መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ስር ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ ማለት ነው፤

16) **“ግዳጅ”** ማለት ማንኛውም የፖሊስ አባል በሲዳማ ብሄራዊ ክልል ውስጥ የሚያከናውነው ማንኛውም የፖሊስ አገልግሎት ነው፤

17) “ልዩ ክህሎት” ማለት የያዘውን ሙያ በቅጥር ወይም በዝውውር በሌላ ፖሊስ አባል ወይም ሲቪል ሠራተኛ በቀላሉ የማይተካ ወይም በገበያ ላይ ማግኘት የማይቻል ልዩ ሙያ ወይም ክህሎት ነው፤

18) **“ጥቅማ ጥቅም”** ማለት ለፖሊስ አባል ወይም

madabanyu damoozi ledotenni woxunni woy danunni uynanni baatooshshe woy jawaachishati;

19) **Poolisete suusa** yaa mittu poolisete miili uurrinshate giddo noosi loosu yawo biilloonyu deerra, qoossosinna gadachosi xawaadu garinni leelishanno balaxote gari noosihu angate mikkitiranna qoteho ayyirinyunni ofollanno kaa’lanchu saajinenni kayise komishiiinerichu geeshsha noo poolisete ayimma suusati;

20) **“Suusu Balaxooshshe”** yaa suusu roorre heera woy taalu suusi hee’reenna mootoo’mate balaxo heera woy taalu suusinna mootoomme heedheenna loosu qeechinni roora woy taalu suusi, mootoommenna loosu qeechi hee’reenna loosu aana keeshshino yannanni roorate;

21) **“Mancho”** yaa kalaqamu woy seeru mannima uynoonnisi bisooti;

22) Koonni lallawi giddo miitu koo/teemanni xawinsoonnihu wole koo/teemano kamaalanno.

## 3. <u>Jeefishshu Mami-geeshsha</u>

Kuni lallawi Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma gashshootu danna giddo Qoqqowu Mootimma biilloonyi hunda ubbanno poolisete assootubba woy poolisete miilla aana hattono garimmasi garinni xaphoomu biddishshi hunda qaxarante loosanno siviilete loosaasine aana loosu aana hosanna.

## 4. <u>Loosu Harinsho Wodhi-woro</u>

Xaphoomu biddishshi loosu harinsho:

ለሲቪል ሠራተኛ ከሥራ ባህርይ አንጻር ከመደበኛ ደመወዝ በተጨማሪ በገንዘብ ወይም በአይነት የሚሰጥ ክፍያ ወይም ማበረታቻ ነው፤

19) **“የፖሊስ ማዕረግ”** ማለት አንድ የፖሊስ አባል በተቋሙ ውስጥ ያለውን የስራ ኃላፍነት የስልጣን ደረጃ መብትና ግዴታ በግልጽ የሚያሳይ ቅደምተከተል ያለው በክንድና በትከሻ በክብር የሚቀመጥ ከረዳት ሳጅን እስከ ኮሚሽነር ድረስ ያለ የፖሊስ መገለጫ ማዕረግ ነው፡፡

20) **“ቀደምትነት”** ማለት የማዕረግ ብልጫ መኖር ወይም እቻ ማዕረግ ኖሮ የሹመት ቅድሚያ መኖር ወይም እቻ ማዕረግና ሹመት ኖሮ በሥራ ኃላፊነት ከፍ ያለ መሆን ወይም እቻ ማዕረግ፣ ሹመትና የሥራ ኃላፊነት ኖሮት በቅጥር ዘመን መብለጥ ነው፤

21) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤

22) በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በክልል መንግስቱ ስልጣን ስር በሚወድቁ ፖሊሳዊ ተግባራት ወይም በፖሊስ ሰራዊት አባላት እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በጠቅላይ መምሪያው ስር ተቀጥረው በሚያገለግሉ ሲቪል ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የአሠራር መርህ</u>

1) Xaphoomu biddishshi tantano deerra deerraho noo sooreeyyenna loosaasine gaamote loosu harinsho qara jeefishshu raga ikkitanno;
2) Gaamote loosu harinsho gutunna halanyu yawo hoodisanno;
3) Xaphoomu biddishshi tantanora deerra deerraho afantanno sooreeyye uynooninsa biilloonyi garinni gumulate yawonsa fulate gadacho noonsa;
4) Xa'mamooshshunna xawaadimmate wodhi-woro harunsitinota ikka noose;
5) Dagate beeqanchimma kaima assitinota ikka noose;
6) Maallada nookki loosu harinsho wodhi-woro harunsa hasiisanose.

**GAFA LAME**

**TANTANO, BIILLOONYENNA LOOSU**

**QEECHA**

5. **Tantanonna Soommanni Gara**
   1) Sidaamu Dagoomi Qoowu Mootimma prezidantichinni soomamanno xaphoomu biddishshi hajajancho;
   2) Qoqqowu poolise jaddo gargarate, jaddote qorto, gashshootinna latishshu, rosunna qajeelshu aantancho xaphoomu biddishsha;
   3) Xaphoomu biddishshi hajajanchi shiqisheenna prezidaantichunni soomantannori konni quwi cinaanchu quwi (2) garinni tantanantino loosu

የጠቅላይ መምሪያው አሠራር፤

1) በጠቅላ መምሪያው መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና የተግባር አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል፡፡
2) የቡድን አሠራሮች የጋራና የግል ኃላፊነትን ያስከትላሉ::
3) በጠቅላይ መምሪያው መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው::
4) የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህን የተከተለ መሆን ይኖርበታል::
5) የሕዝብ ተሳትፎን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት::
6) የገለልተኝነት የአሠራር መርህን የተከተለ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለአደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር**

5. **አደረጃጀት እና አሿሿም**

1) በሲዳማ ብሔራዊ ክልልመንግስት ርዕሰ መስተዳደር የሚሾም የጠቅላይ መምሪያ አዛዥ፤
2) የክልል ፖሊስ ወንጀል መከላከል፣ ወንጀል ምርመራ፣ አስተዳደር ልማት፣ ትምህርትና ስልጠና ም/ጠቅላይ መምሪያ፣
3) በጠቅላይ መምሪያ አዛዥ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተደራጀውን የስራ

golla massaganno aantancho xaphoomu biddishshi hajajaano;

4) Poolisete wolqa miilla; nna
5) Hasiisannoha ikke leelliro siviile loosaasine heedhannosi;
6) Konni quwi cinaancho quwi (2) worroonnihu noo gedeenni hasiishshu garinni wolootu tantanubba heedhasira dandiitanno;
7) Zoonetenna zoonete deerrinni noo Quchumu gashshooti poolisete biddishshi sooreessi xaphoomu biddishshi hajajanchi shiqisheenna Qoqqowu suumumenni zoonete qaru gashshaanchi woy Quchumu gashshooti kantiiwinni soomamanno.
8) Woradunna woradu deerinni noo tantano poolise borro mini sooreeyye xaphoomu biddishshi hajajanchi shiqisheenna zonete qaru gashshaanchi sumuumenni xaphoomu biddishshi hajajanchinni soomantanno.

ክፍል የሚመሩ ምክትል የጠቅላይ መምሪያ አዛዦች፤

4) የፖሊስ ሰራዊት አባላት፤ እና
5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲቪል ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች የአደረጃጀቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡
7) የዞን እና በዞን ደረጃ ያለ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ በጠቅላይ መምሪያ አዛዥ አቅራቢነት በክልሉ ፕረዝዳንት ይሁኝታ መሠረት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ይሾማል፤
8) የወረዳ እና በወረዳ ደረጃ ያለ አደረጃጀት ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በጠቅላይ መምሪያ አዛዥ አቅራቢነት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ይሁኝታ መሰረት በጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ይሾማሉ፡፡

## 6. Hundaanchimma

1) Xaphoomu biddishshi hundaanchimma Qoqqowu prezidantichira ikkitanno.
2) Zoonetenna zoonete deerinni noo Quchumu gashshooti poolisete biddishshi hundaanchimma balaxonsa garinni zoonete qaru gashshaanchira woy Quchumu kantiiwiranna xaphoomu biddishira ikkanno.
3) Woradunna woradu deerrinni noo tantano poolisete borro mini hundaanchimma woradu

## 6. ተጠሪነት

1) የጠቅላይ መምሪያው ተጠሪነት ለክልሉ ፕረዝዳንት ይሆናል፤
2) የዞን እና በዞን ደረጃ ያለ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ ተጠሪነታቸዉ እንደቅደም ተከተላቸዉ ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ለከተማው ከንቲባ እና ለጠቅላይ መምሪያው ይሆናል፡፡
3) የወረዳ እና በወረዳ ደረጃ ያለ አደረጃጀት ፖሊስ ጽ/ቤት ተጠሪነት ለወረዳዉ ዋና

qaru gashshaanchira woy siinu quchumi gashshaanchiranna zoonete woy Quchumu gashshooti poolisete biddishshira ikkanno.

4) Konni quwira cinaancho quwa (2)nna (3) worroonnihu noo gedeenni heerenna zoonenna zoonete deerrinni noo Quchumu gashshooti poolisete biddishshinna woradunna woradu deerrinni noo tantano poolisete borro mini barra barranko heeranonsa loosu millimillo lainohunni hundaanchimmansa xaphoomu biddishshira ikkanno.

## 7. <u>Qoqqowu poolisete Wolqa Sokka</u>

1) Qoqqowu giddo dagate ga’labbo, keerunna keeranchimma agaramase buuxa;

2) Qoqqowunna federaalete seeri garinni jaddo gargara, buuxanna qorqora;

3) Qoqqowu mootimmanni fultanno seerubbanna gumulo ayirisiisa;

4) Qoqqowu giddo hallanyootu lubbote, bisu keeeranchimma, jajjanna bayriidi seerinni uyinooninsa qoosso agara;

5) Seerunni fajjinannihu garinni federaalete Mootimma biilloonyi hunda ubbanno jaddo gargaratenna qorqorate federaalete poolisenna wolootu federaalete uurrinshubba ledo halante loossanno;

6) Qoqqowu Mootimma uurrinshubbara, xintu latishshubbaranna albiidi massagaanora agarooshshenna gargarooshshe aa;

አስተዳዳሪ ወይም ለክፍለ ከተማው ዋና አስተዳዳሪ እና ለዞኑ ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ፖሊስ መምሪያ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን እና በዞን ደረጃ ያለ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያና የወረዳ እና በወረዳ ደረጃ ያለ አደረጃጀት ፖሊስ ጽ/ቤት የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በተመለተ ተጠሪነታቸው ለጠቅላይ መምሪያው ይሆናል፡፡

## 7. <u>የክልሉ ፖሊስ ሠራዊት ተልዕኮዎች</u>

1) ክልሉ ውስጥ የህዝብ ፀጥታ፣ ሰላም እና ደህንነት መጠበቁን ማረጋገጥ፤

2) በክልል እና በፌደራል ህጎች መሰረት ወንጀሎችን መከላከል፣ መመርመር እና መቆጣጠር፤

3) በክልሉ መንግስት የሚወጡ ህጎችን እና ውሳኔዎችን ማስከበር፤

4) በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችን ሕይወት፣ አካላዊ ደህንነት፣ ንብረት እና ሕገ መንግሥታዊ መብቶችን መጠበቅ፤

5) በሕግ በሚፈቅደው መሠረት በፌዴራል መንግስት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመመርመር ከፌዴራል ፖሊስና ከሌሎች የፌዴራል ተቋማት ጋር ተባብሮ መስራት፤

6) ለክልሉ የመንግስት ተቋማት፣ መሰረተ ልማቶች እና ከፍተኛ ባለስልጣናት ጥበቃና ከለላ መስጠት፤

7) Dagooma hanqaffino poolise lossa, dagate hedo lossanna qarqaru daga, budu uurrinshubbanna wolootu halamaano bissa ledo halamatenni jaddo gargarate hayubba aana beeqqa;

8) Kalaqamu woy mannu loosino hedewelcho dano, cancunna keeranchimmate danora rahote dawaro aate qixxaabbinota ikka;

9) Rosunna qajeelshunni poolisete wolqa dhuka dhaabachisha;

10) Baalanta assootubba bayriidi seeri, manihiimate qoosso wodhi-woronna ogimmate akatome aana worroonnihu garinni loosa.

## 8. <u>Xaphoomu Biddishshi Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Xaphoomu Poolisete Biddishshi Dagoomu hasattonna beeqqo mereersinoha balaxotenni jaddo gargarate amanyoote ha'runsatenni loosannoha ikkanna konni woroonni noohu biilloonyinna loosu qeechi noosi:

1) Baayriid Seerinna Seeru amuraati, Mootimmanna Gobboomu adawinna Mannihiimmate qooso aana loosantanno jaddonna lawinoha yaaddote assoote gargaranno, Qorto buuxanno;

2) Qoqqowu Mootimma uurrinsha agaranno, Jajjabba Qoqqowu Mootimma biilla,

7) የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስን ማሳደግ፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እና ከአካባቢው ማህበረሰቦች፣ ባህላዊ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ወንጀልን የመከላከል ስልቶች ላይ መሳተፍ፤

8) ለተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ድንገተኛ አደጋዎች፣ ለሁከት እና የደህንነት አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆን፤

9) በትምህርትና ሥልጠና የፖሊስ ሠራዊትን አቅም ማጎልበት፤

10) ሁሉንም ተግባራት በህገ መንግስቱ፣ በሰብአዊ መብቶች መርሆች እና በሙያ ስነምግባር ላይ በተደነገገው መሰረት ማከናወን።

## 8. <u>የጠቅላይ መምሪያው ሥልጣንና ተግባር</u>

የሲዳማ ብሄራዊ ክልል መንግስት ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በህብረተሰቡ ፍላጎትና ተሳትፎ ያረጋገጠ ወንጀልን አስቀድሞ የመከላከል መርህን ተከትሎ የሚሰራ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1) በሕገ-መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ፣ በመንግሥትና በሀገር ፀጥታ እና በሰብዓዊ መብት ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውም ዓይነት የወንጀል ስጋቶችና ድርጊቶችን በማንናውም በክልሉ አስተዳደር ወሰን ይከላከላል፣ይመረምራል፤

2) የክልሉ መንግሥት ተቋማትን ይጠብቃል፤ ለከፍተኛ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት፣

Federaalete Mootimma Ayirrinyu wosinanna Dippiloomaatete agaarooshshunna dukkishu Owaante aanno;

3) Qoqqowu daga horo kissanno hajubba aana wole qoqqowubba qasiiso qooxeessira loosantanno gashshootu danna sa’e loosantanno jaddonna hattonni Qoqqowu giddoonni jaddo loosse wole qoqqowo hadhino huluullamaano qoqquwubbate ledo assinanni gutu sumuumme xintinni seeru hundaanni hosiissanno; Qorto buuxxanno;
4) Ga’labbote huluulo heedhuronna jaddote assooti jeefamara dandaannota huluullamate ikkadu korkaati heerironna assoote gargarate faashsho assa hasiissannota ikkase ammanniro huluullammoonni qooxeessira leeltanno kaameellanna lekkaancho uurrisatenni hedeweelcho faashsho assanno; Huluullamaano mannootanna naaqashe amadatenni buuxanno;
5) Qoqqowu Yoo Minna biilloonyi hundaanni noorenna Federaalete Seeri xintinni lekkishshunni Qoqqowu Mootimmara uynoonniha jaddote assoote gargaranno, buuxanno, rorrimmatenni massaganno; jaddote qorto seeru xintinni gumulamasi buuxanno; farcote biiro ledo qinaawe loosanno;
6) Hasiisannoha ikkiro Zoonete woy Quchumu gashshooti poolise wolqa uurrinshara lekkishshu biilloonye aanno.Gumulshu rippoorte adhanno;

የፌዴራልመንግስት ክብር እንግዶች እና ለዲፕሎማቶች የጥበቃ እና እጀባ አገልግሎት ይሰጣል፤

3) የክልሉ ህዝብ ጥቅሞች በሚነኩ ጉዳዮች ላይ ከአጎራባች ክልሎች አከበቢ የሚፈፀሙ ማናቸውንም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን እንዲሁም በክልላችን ወንጀል ፈፅመው ወደ ሌላ ሌላ ክልል የሄዱ ተጠርጣሪዎችን ከየክልሎቹ ጋር በሚደረግ የጋራ ስምምነት መሠረት በቁጥጥር ስር ያውላል ፤ይመረምራል፤

4) የፀጥታ ስጋት ሲኖርና የወንጀል ድርጊት ሊፈፀም እንደሚችል ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖርና ድርጊቱንም ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት በተ ጠረጠረው አካባቢ የተገኙ ተሽከርካሪዎችና እግረኞችን በማስቆም ድንገተኛ ፍተሻ ያደርጋል፤ ተጠርጣሪ ሰዎችና ማስረጃዎችን በመያዝ ይመረምራል፤

5) በክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር በሚወድቁ እና በፌዴራል ሕጎች መሠረት በውክልና ለክልል መንግስት የተሰጡ የወንጀል ድርጊቶች ይከላከላል ይመረምራል በበላይነት ይመራል፤ የወንጀል ምርመራ በህግ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ከፍትህ ቢሮ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

6) አስፈላጊ ሆኖ ስያገኘው ለዞን ወይም ለከተማ አስተዳደር ፖሊስ ሠራዊት ተቋማት የውክልና ስልጣን ይሰጣል፤ የአፈጻጸም ሪፖርት ይቀበላል፤

7) Qoqqowunna Dagoomu aana jawa eddaro iillishannoti jaajjabba jaddonna Shibbirete jaddo yaaddo heedhuro baxxitinota jaddote qorto taje gamba assate hayyo horonsiratenni hasiisannoha ikke leelliro xa'mosi xaaddotenni Yoote Minira shiqishanno; hajajote garinni gumulanno.

8) Poolise winaamu ikkito xaadduro Xaphoomu hajajaanchi fajjonni Yoote Mini hajajo nookkiha baxxitino buuxote hayyonni mashalaqqe gamba assa dandaanno,Ikkeennano Yoote Mini hajajo nookkiha gamba assinoonni tajenna korkaata Xaphoomu Hajajaanchi uynota yannate geeshshi fajjo ledo 48 sa'ate gido Yoote Minira borrotenni shiqisha noosi.

9) Fooreensikete Qorto laabiraatoore tantananno; Qorqoranno; Massaganno; xa'maitanno bissara dawaro aanna woy Ogimmate naqaashe aanno.

10) Qoqqowu Mootimma gashshitinno qara qara doogo aana Tiraafiikete Wodho ayirrisamase qorqorqonno Doogote aani Tiraafiiket dano pilaane kaaysanno; Buxxanno;

11) Egzibiitete amadamino uduunnicho tajimmate ikkannokkiha woy konni ledo raggete dandiisiisannokkiha Mannu ooso fayyimma aana jawa eddaro iillishshanno, ba'annohanna amadooshshehono mitiinsannoha woy luphiima fulo abbannoha ikkiro farcote biiro ledo hasaawe akeekishsha ha'ratenni woy wole doogonni soorrote naqaashe heedhanno gede assatenni uduunnicho uduunnichu annira

7) በክልሉ እና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከባድ ወንጀል እና የሽብር ወንጀል ስጋት ሲኖር ልዩ የወንጀል ምርመራ ማስረጃ የማሰባሰብ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ስገኝ ጥያቄውን በቀጥታ ለፍ/ቤት ያቀርባል በትዕዛዙ መሠረት ይፈፅማል፡፡

8) ፖሊስ አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው በጠቅላይ አዛዡ ፍቃድ ያለፍ/ቤት ትዕዛዝ በልዩ ምርመራ ዘዴ ማረጃ ልሰበስብ ይችላል ሆነም ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ የተሰበሰበው ማስረጃ በ48 ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና በጠቅላይ አዛዡ የጠሰጠው ጊዜያዊ ፍቃድ ጨምሮ ለፍ/ቤት በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9) የፎረንሲክ ምርመራ ላብራቶሪዎችን ያደራጃል፤ይቆጣጠራል፤ይመራል፤ለጠያቂው አካል ምላሽ ይሰጣል ወይም የሙያ ምስክርነት ይሰጣል፡፡

10) የክልሉ መንግስት በምያስተዳድራቸው ዋና ዋና መንገዶች ላይ የትራፊክ ደንብ መከበሩን ይቆጣጠራል የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ፕላን ያነሳል፤ ይመረምራል

11) በኤግዚቢትነት የያዘውን ዕቃ በማስረጃነት የማያገለግል ወይም በህ መሠረት ሊወረስ የማይችል በሰው ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት የምያደርሱ የምበላሹ ለአያያዝ አስቸጋሪ ወይም ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል ከሆነ ከፍትህ ቢሮ ጋር በመነጋገር ናሙና በመውሰድ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ተለዋጭ ማስረጃ እንዲኖር በማድረግ ዕቃውን ለባለንብረቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ መስጠት

higanno gede hajajo aate woy uduunnichu hi'ramee Yoote Mini hajajo aa geeshsha woxu mootimmate shallaggora ofollanno gede assanno.

12) Konni quwi cinaanchu quwi (11) aana ofoshshinshoonniri agaramino garinni hee'reenna Egzibiite ikka dandaanno yine amandoonnihu aye uduunnichi egzibiite ikka hoogasinna tajimmate kaa'lannokkiha ikkasi buuxanturo annaho qollanni gede assanno.

13) Poolisete wolqa Tantanonna Owaantete aamooshshi deerra; Poolisete wolqa miilla filanna gaamooshshe,Rosunna qajeelshu,Horo, Geego, Suusu aa, Wodhote uddanno uddi'ra, Qodhonna wole labbanno hajo aana gobboomu Istaandaarde safaraanchi xintinni gumulanno.

14) Qoqqowunnita Jaddo gargarannitanna Qortota istiraateejje qixxeessanno loosu aana hosaseno buuxanno;

15) Poolisete miillara rosu woy suusunni damooza baantanniha ikke hee'reenna addi addi horonna abella xiinxallatenni qoqqowu mootimmara shiqishanno, fajjiniro loosu aana hosiisanno;

16) Poolisete wolqara rosunna qajeelshu uurrinsha qoqqowoho baabbaxxitino basera Uurrisanno, Istaandaarde fushshanno loosiishshano ha'runsanno;

17) Poolisete miillara hasiissannota loosu simirrite aanno; ha'runsanno qorqoranno rippoorte adhanno;

18) Poolisete owaantera kaa'litanno CCtive kaameerranna addi addi Tekinoloojje guma

ወይም ንብረቱ ተሸጦ ፍ/ቤቱ ውሳኔ እስኪሰጥ ገንዘቡ በመንግስት ሂሳብ ተቀማጭ ያደርጋል፡፡

12) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (11) የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ ኤግዚቢት ሊሆን ይችላል ተብሎ የተያዘ ማንኛውም ንብረት ኤግዚቢት አለመሆኑን ወይም በማረጃነት የማይጠቅም መሆኑ ከተረጋገጠ ለባለንብረቱ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

13) የፖሊስ ሰራዊት አደረጃጀትና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ፤ የፖሊስ ሰራዊት አባላት ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ሥልጠና፣ እና ጥቅማጥቅም፣ስንብት፣ በማዕረግ አሰጣጥ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በትጥቅና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ሀገር አቀፍ ስታንዳርድ መሠረት ይፈፅማል፡፡

14)የወንጀል መከላከልና ምርመራ ክልል አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል ተግባሪዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

15)ለፖሊስ አባላት በትምህርት ወይም በማዕረግ ደመወዝ የሚከፈል ሆኖ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅምና አበል አጥንቶ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16) የፖሊስ ሰራዊት ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በክልሉ በተለያዩ አካባቢ ያቋቁማል፣ ስታንዳርድን ያወጣል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

17)የፖሊስ አባላት አስፈላጊውን የስራ ስምሪት ይሰጣል ይከታተላል ይቆጣጠራል ሪፖርት ይቀበላል፤

18) ለፖሊሳዊ አገልግሎት የሚረዱ የሲ.ሲ.ቲቪ

halashshanno, ho’ronsiranno hasiissanno basera woranna, qorqoranno;

19) Konni cinaanchu quwi (18) aana ofoshshinshoonniri agaramino garinni hee’reenna Mootimma woy mootimaame ikkitinokki uurrinshubba woy hallany wodhinohu CCtive kaameeri woy aye Tekinoloojje jaddo gargaratenna Qortote loosira hasiisannoha ikkiro owaante baatooshshiweello afiranno;

20) Poolisete miillanna maatera hikkiminnu owaante uytanno uurrinshubba qoqqowu giddo babbaxxitino zoonna qooxeessira uurrisanno hasiisannoha ikkiro Poolisete miilla Gobbate gobbaanni akka’mitanno gede tola ikkito qineessanno Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

21) Poolisete miillanna Siwiile loosaasine owaante uytanno biironna kaampe hee’nanni minna ijaartanno gede assanno.

22) Keere ayirrisiisate sokko woy wole Gobboomu sokkora bobbakkanno woy gaammantanno poolisete miilla Federaaletenni uynanni kooti garinni bobbaasanno;

23) Motorete kaameela oofate dandisiisanno qajeelsha poolisete miillaranna siwiilete loosaasinera aanno. Hadhishshu biillonyinni uynoonni ikkadimmate buuxishshi taje xintinni oofate fajjo aanno;

24) Konni cinaanchu quwi (23) aana ofoshshinshoonniri agaramino garinni

ካሜራዎችን ወይም ልዩ ልዩ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን ያስፋፋል ይጠቀማል ተገቢ በሆኑ ቦታዎች ይተክላል ፤ይቆጣጠራል፤

19)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (18) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ የተተከለ ሲ ሲ ቲቪ ካምራ ወይም ማናቸውም ቴክኖሎጅ ለወንጀል መከላከልና ምርመራ ተግባር አስፈለጊ ሆኖ ሲገኝ አገለግሎትን በነጻ ያገኛል፤

20)ለፖሊስ አባላትና ቤተሰብ የህክምና አገለግሎት የሚሰጡ ተቋማት በክልሉ በተለያዩ ዞኖች አከባቢ ያቋቁማል አስፈላጊ ሲሆን የፖሊስ አባላትን በውጪ ሀገር ኢንዲታከሙ ሁኔታ ያመቻቻል፤ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

21)የፖሊስ አባላት እና ሲቪል ሠራተኞች አገለግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ቢሮዎች ካምፖች የመኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ያደረጋል፤

22)ለሠላም ማስከበር ተልዕኮ ወይም ሌላ ሀገራዊ ተልዕኮ የሚሠማራ ወይም የሚመደብ የፖሊስ አባላትን ከፌዴራል በሚሠጠው ኮታ መሠረት ያሰማራል፤

23)ባለሞተር ተሽርካሪ መንዳት የሚያስችል ሥልጠና ለፖሊስ አባላት እና ሲቪል ሠራተኞች ይሰጣል፡፡ በትራንስፖርት ባለስልጣን በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት መሠረት የመንጃ ፈቃድ ይሰጣል፡

24)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (23) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

hee’reenna hasiisannoha ikkiro Mootimmate loosi minnara Oofaanchimmate owaante uytanno loosu sooreeyyera oofate ikkadimma buuxishshita oofate fajjo aanno;

25) Uurrinshate Sokko ledo amadaminohunni Poolisete wolqa Miidiya tantananno, Massaganno; Ha’runsanno, seesi-qalonna addi addi loossara fajjo aanno; Ha’runso assanno hasiisannoha ikke leelliro Seerunni xa’mantanno gede assanno;

26) Ispoortennita Seesi-qalote kibebenna miilla Mannimmate guunte ispoorte loossanno mereershuwa tantananno; Gashshanno;

27) Poolisete miillata dagoomitte heeshsho mitiimma tira dandisiissanno kibebba meddebire; Maamaranna Fawundeeshiine tanatananno; Tittirshu jirtetenni gumulamanno;

28) Poolisete wolqa owaantera hassanno ijaarra loossanno woy Kaameela gatamartanno uurrinsha tanatananno; Urrisanno;

29) Poolisete miillanna Siwiilete loosaasine loosu ledo xaadino hajonni Jaddotenni woy Fitaabeeretenni kassasanturo woy gargarate kisse hanafate Uurrinshanniha higgete ogeessa gaamatenni woy ayyaayamaancho gaamatenni ayyaayamate owaante afi’dhanno gede assanno;

30) Zoonnatenna Quchumu gashshootira Poolisaawe hajo aana Tekinikaalenna addi addi kaa’lo assanno;

ለመንግስት መስሪያ ቤቶች በአሽርካረነት አገለግሎት ለሚሰጡ ለሥራ ኃላፍዎች የአሽከርካርነት የብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፈቃድ ይሰጣል፤

25)ከተቋሙ ተልዕኮ ጋር በተያያዘ የፖሊስ ሠራዊት ሚዲያ ያደራጃል፣ ይመራል፤ ይከታተላል፣ ክነ-ጥበብ እና ልዩ ልዩ ሥራዎች ፈቃድ ይሰጣል፤ ክትትል ያደረጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በህግ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

26)የስፖርት ኪነ-ጥበብ ክበባት እና አባላት የስፖርት ማዘውተሪያና መበለጸጊያ ማዕከላት ያደረጃል፤ ያተዳድራል፤

27)የፖሊስ አባላትን ማህበራዊ ችግር ሊቀርፍ የሚጭል ክበባትን መደብር፤ማህበር እና ፋውንዴሽን ያደራጃል፤ ዝርዝሩ በደምብ ወይም በመመሪያ ይወሰናል፤

28)ለፖሊስ ሠራዊት አገለግሎት የሚውሉ ህንጻ የሚሠሩ ወይም ተሽከሪካሪ የሚጠግኑ ተቋማት ያደረጃል፤ያቋቁማል፤

29)ለፖሊስ አባል እና ሲቪል ሠራተኛ ከመደበኛ ሥራ ጋር በተገናኘ በወንጀል ወይም በፍትሀብሄር ሲከሰሱ ወይም በመከላከል ክስ ለመመስረት የተቋሙ የህግ ባለሙያ በመመደብ ወይም ጠበቃ በመቅጠር ነጻ የጥብቅና አገለግሎት እንዲያገኙ ያደራጋል፤

30)በዞኖች ወይም በከተማ አስተዳዳር ፖሊሳዊ ጉዳዮች ላይ ቴክንካል እና ልዩ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

31) Qoqqowu Yoo Minna biilloony hundaanni ubbanno jaddonni huluullammanni hallanyootann gaamo hallanyootann gaamo Yoote Mini hajajonni hiikkuno qoqqowu Danni giddoonni amadate biillonyu noosi;

32) Qoqqowu daga keeraate danote aana tugganno jaddo gargarate woy Qorto buuxate kaa'lannoha ikkasi ammaniro hiitte mashalaqqeno aye manchiwaayinni adhanno: Tittirshu biddisunni gumulamanno;

33) Qoqqowunniha jaddote rikkerdenna Qansootu ashaara mereerishaho tanatane amadanno, Ho'rote aana hosiisanno; Taje aanno;

34) Qoqqowunnita Jaddonna Tiraafiikete dano mashalaqqe gamba assanno; Tittiranno; Korkaata badanno jaddote dana badatenni tittirsha aanno; Hajo la'anno bissara fincanno;

35) Hedeweelcho kalaqamunna mannau loosino dano kalaqanturo keerenna ga'labbo agarisiisatenni godda'antino mannoota kaa'late Dagoomuniwaayinni Mootimmaamenna motimmannita ikkitinokki uurrinshanna maammara ledo haalamatenni loosanno; Buuxanno; reeshshunna gadda'antinor ayimma badanno Naqaashe aanno;

36) Agarooshshu owaante aate loosira bobbaha hasidhanno hallanyu uurrinshara ikkadimmate buuxishshi taje aanno,Haroonsanno; ha'runsanno; Faaqanno;

37) Zoonenite woy Quchumu gashshooti poolisenni hanaffino qorto woy Qorto hanaffanno gede; Hanafantino jaddote qorto aana ha'runsote

31)በክልሉ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የወንጀል ድረጊት የተጠረጠረ ግለሰብ ወይም ቡድን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በየትኛውም የክልሉ ወሰን ውስጥ የመያዝ ስልጣን አለው፤

32)የክልሉ ብሄራዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል ለመከላከል ወይም ለለመርመር የሚረዳ መሆኑ ከታመነበት ማንኛውም መረጃ ከማንኛውም ሰው ይወሰወዳል፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

33) ክልል አቀፍ ወንጀል ሪከርድ እና የዜጎች አሻራ በማዕከል አደራጅቶ ይይዛል፣ጥቅም ላይ ያውላል፤ማስረጃ ይሰጣል

34)የወንጀልና የትራፊክ አደጋ ክልል አቀፍ መረጃ ይሰበስባል፤ይተነትናል፤መንስኤውን ይለያል የወንጀል ዓይንት በመለየት ትንታኔ ይሰጣል፤ለሚመለከተው ያሰራጫል፡፡

35)የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ሠላምና ጸጥታ በማስፈን የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት ከህብረተሰቡ እና ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤ይመረምራል፤የሚችን ወይም የተጎጂዎችን ማንነት ይለያል፤ማስረጃ ይሰጣል፡፡

36)የጥበቃ አገለግሎት በመስጠት ሥራ ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ የግል ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ያድሳል፤ይከታተላል፤ይሰርዛል፡፡

37)በዞን ወይም ከተማ አስተዳደር ፖሊስ የጀመረው ምርመራ ወይም ምርመራ እንዲጀመር፣ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ

rippoorte shiqqanno; Jaddote qorto loosiishsha Seeru xintinni ha'rasinna hoogasi buuxanno, Qortote mazigawi aana hasiissanno hajajo aanno;

38) Hiikkuno ayirrinyunni geegiissantino poolisete miilla Gobbate roorrimma qooso jiffanno ikkito xaadduro babbaxxino korkaatinni haaro qujeelsha uyne foonqe diwa dandiinaayikkiha ikkiro poolisete wolqara marro woshshatto assa dandaanno:

39) Konni cinaanchu quwi (38) aana ofoshshinshoonniri agaramino garinni hee'reenna marro assinoonni woshshatto garinni poolisete uurrinshsha karsamino poolisete wolqa miila uurrinshsha hasiisannoha ikkasi ammanturo albillichote owaatara noosi suusinni qaxarara dandaanno; Tittirshu biddisunni gumulamanno;

40) Hiikkuyno Yoote Mini hajajonna murote gumulu iillituro Jeefisanno; Jeefisiisanno.

41) Wolu seerinni uynoonnisi biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno,

42) Olu bagado seeru garinni qorqoranno, gashshanno, qodhisiisanno, fajjo aanno, rigidanno;

43) Jajju anna ikkanno; Wule eanno, Su'misinni kassassatenna kassasamate dandaanno.

**9. <u>Xaphoomu Biddishshi Hajajanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

1) Konni lallawira quwa 8 hunda worroonni biilloonyenna loosu qeecha aliidimatenni massaganno, irkisanno, qorqoranno,

የክትትል ሪፖርት እንዲቀርብ፣ የወንጀል ምርመራ በሕግ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በምርመራ መዝገብ ላይ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

38)ማንኛውም በክብር ለተሰናበቱ የፖሊስ አባላት የሀገር ልዓላዊነትን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲያጋጥም በተለያየ ምክንያት አዲስ ስልጠና በመስጠት መሸፈን የማይቻል ሲሆን ለፖሊስ ሠራዊት አባል ዳግም ጥሪ ሊያደርግ ይችላል፡

39)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (38) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዳግም ጥሪ መሰረት ወደ ፖሊስ ተቋም የተቀላቀለ የፖሊስ ሠራዊት አባል ተቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በቀጣይነት ሊያገለግል በነበረበት የማዕረግ ደረጃ መልሶ ሊቀጥረው ይችላል፤ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

40) ከማናቸውም ፍርድ ቤት ትዕዛዝና ውሰኔ ሲደርሰው ይፈጽማል፤ያስፈጽማል፡፡

41) በሌላ ህግ የተሰጠውን ሥልጠንና ተግባተር በሥራ ላይ ያውላል፣

42) የጦር መሳሪያ በህግ መሠረት ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣ የስታጥቃል፣ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፤

43) የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ውል ይዋዋላል፤በስሙ ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላል፤

**9. <u>የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ ስልጣንና ተግባር</u>**

1) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 ሥር የተደነገጉትን ሥልጣንና ተግባር በበላይነት ይመራል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

taashshote qaafo a'dhanno;

2) Istraatejike massagaano suusu lopho Qoqqowu prezidaantichira shiqishe soomanniha assanno;
3) Poolisete miilla massagantanno Wodho burqisanno hajo la'anno bisinni kaajjituro loosu aana hosiisanno;
4) Addi addi biddisubba burqisanno, kaajjishanno loosu aana hosiisanno; qorqoranno;
5) Uurrinshanniha loosu pirogiraame fushshanno, loosu aana hosase harunsanno, taashshote qaafo a'dhanno;
6) Uurrinshate baajete mootimmate shiqishanno, fajjiniro seeru garinni gashshanno;
7) Zoonetenna Quchumu gashshooti poolisete uurrinshubba loosu mixonna jeefishsha haaranno, gutu songo massaganno, keenanno, gumulanni gumulo jeefishsha harunsanno, taashshote qaafo a'dhanno;
8) Gutu songo winaamu gambooshshe aye yannarano woshshara dandaanno;
9) Muishu jaddonni woy qoqqowu mootimma keeranchimma aana aliidi fojo fincatenni huluulamoonnisi mancho baankete shallago harancho yanna giddo shallagote millimillo qorqorantannonna guma xawinsanni gede hajo la'annosi faynaansetenna federaalete uurrinshubba ledo qinaawe loosanno;
10) Gobbatenna dagate aana jawa gawajjo iillishara dandaanno jawa jaddonna shibbirete

2) ኢስትራቴጂክ አመራሮች የማዕረግ ዕድገት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቅርቦ ያሾማል፣
3) የፖሊስ አባላት የሚመሩበትን ደምብ ያመነጫል በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
4) ልዩ ልዩ መመሪያ ያመነጫል፣ ያፀድቃል ሥራ ላይ ያውላል ይቆጣጠራል፣
5) የተቋሙን የስራ ዕቅድ ያወጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣
6) የተቋሙን በጀት ለመንግስት ያቀርባል ሲፈቀድም በህግ መሠረት ያስተዳድራል፣
7) የዞንና የከተማ አስተዳደር የፖሊስ ተቋም የስራ ዕቅድና ክንውን ይቀበላል፣ የጋራ ጉባኤውን ይመራል ይገመግማል የሚወሰነው ውሳኔ ተግባራዊነቱ ይከታተላል የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣
8) የጋራ ጉባኤ አስቸኳይ ስባሳባ በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፣
9) በሙስና ወንጀል ወይም በክልሉ መንግስት ደህንነት ላይ ከፍተኛ ሚስጥር በማባከን የተጠረጠረ ሰው የባንክ ሂሳብ በአጭ ጊዜ ውስጥ የሀሳብ እንቅስቃሴ እንዲመረመር እና ውጤቱ እንዲገለጽለት ጉዳዩ ከሚመለከተው የፋይናንስ እና የፌዴራል ተቋም ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
10) በሀገር እና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከባድ ወንጀል እና ሽብር ወንጀል ሥጋት ሲኖር ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ

jaddo huluullo heedhuro yoote mini hajajo nookkiha qoqqowoho aye qooxeessira hedeweelcho faashsho assinanni gede hajajara dandaanno ;

11) Gobbate horonna keeranchimma gargarate yaatenni jwa fojooti yee amnadino uurrinshate hasiisannore ikkinon uduunni hiro shallagote tajenna sanade mashalaqqe gamba assate fultanno baatooshshu taje xawinsanikki gede assara dandaanno; tittirsha seerunni gumulanni;

12) Konni quwira cinaancho quwa (11) worroonnihu heerirono yoote mini hajajiro woy qoqqowu amaale mini baxxino garinni xa’miro leellishate gadacho noosi;

13) Aliidi massagaano suusu lopho fultanno Wodho garinni aanno;

14) Hasiisannoha ikke leelliro biilloonyesinna loosu qeechasi bocunni woy wo’munni wo’ma aantano xaphoomu biddishshi hajajaanora aara dandaanno;

15) Uurrinshate giddo babbaxitino boordete miilla soomanno.

**10. Aantanchu Xaphoomu Biddishshi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1) Loosu mixira, tantanateninna qineesatenni komishiinerichu ledo ka’lame loosanno;

2) Mereerimma massagaanora suusa ledanno mootonsanno;

3) Kaimu massagaanora suusu lopho buuxanni kaajjishanno;

በክልሉ በየትኛውም አከባቢ ድንገተኛ ፍተሻ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፤

11) ሀገራዊ ጥቅምና ደህንነት ለመከላከል ሲባል ጥብቅ ሚስጥር ብሎ የሚሰይማቸውን ለተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ የቁሳቁስ ግዥ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ለመረጃ ማሰባሰብ የሚወጡ የክፍያ ማስረጃዎች እንዳይገለጹ ሊያደረግ ይችላል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

12) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (11)የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ወይም በክልሉ ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤

13) የከፍተኛ አመራር የማዕረግ ዕድገት በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሰጣል፤

14) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ወይም በሙሉ ለም/ጠቅላይ መምሪያ አዛገች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

15) በተቋሙ ውስጥ የተለያዩ የቦርድ አባላት ይሰይማል፤

**10. ምክትል ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ሥልጣንና ተግባር**

1) የክፍሉን ሥራን ማቀድ፣ማደራጀትና በማስተባበረት ከጠቅላይ መምሪያ አዛዡ ጋር በመተባበር ይሰራል፤

2) የመካከለኛ አመራር የማዕረግ ዕድገት ይሰጣል፤

3) ጀማሪ አመራር ማዕረግተኛ የማዕረግ ዕድገት እየመረመረ ያጸድቃል፤

4) Xaphoomu biddishshi hajajanchi bade aanno wole loossa loosanno;
5) Xaphoomu biddishshi Hajajanchi baxxino garinni lekkisha uyikkinni madabanyu loosi aana heeranokki yannara jaddo gargarate aantanchu biddishshi aantanchu komishiinerichi riqiwe loosanno;
6) Biilloonyisi kayise hundasiinni noo massagaanora lekkisha aanno;

**11. <u>Manaajimentete Komite Miilla</u>**

Xaphoomu biddishshi manajimentete miilla:

1) Xaphoomu biddishshi hajajanchi……………………Gambisaancho;
2) Aantanchu xaphoomu biddishshi hajajaano……………………..Miila;
3) Xaphoomu biddishshi hajajanchi borro mini sooreessi…………….Borreessancho ikkanno.
4) Konni quwira cinaancho quwa (1) kayise (3) geeshsha worroonnihu noo gedeenni heerenna komishiinerichunni gamamanno wolu sooreessi woy hajo xawisannoha huuro aannoha woy huuro aannokkiha ikke manaajimentete miila assara dandaanno

**12. <u>Manaajimentete Komite Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

1) Uurrinshate baajettete hasatto kaajjishe qoqqowu mootimmara shiqishanno, jeefishsha harunsanno;
2) Qodhote hiro hasatto hasaabbe kaajjishanno;
3) Qoqqowu poolisete wolqa diru mixo aana hasaabbe kaajjishanno;
4) Qoqqowu poolisete tantanonna owaantete amamooshshi deerra, poolisete miilla filanna qaxara, rosunna qajeelishu, damoozanna

4) በጠቅላይ መምሪያ አዛዡ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
5) የጠቅላይ መምሪያ አዛዡ በተለየ ሁኔታ ውክልና ሳይሰጡ በመደበኛ ስራቸው ላይ በማይኖሩበት ጊዜ የወንጀል መከላከል ም/ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ተክቶ ይሠራል፤
6) ከሥልጣኑ ቀንሶ ከስሩ ላሉ አመራሮች ውክልና ይሰጣል፡፡

11. <u>የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት</u>

የጠቅላይ መምሪያ የማኔጅመንት አባላት፤

1) የጠቅላይ መምሪያ አዛዡ………ሰብሳቢ፤
2) ም/ጠቅላይ መምሪያ አዛገሮች…አባላት፤
3) የጠቅላይ መምሪያ አዛዡ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ፀኃፊና አባል ይሆናል፡፡
4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላይ መምሪያ አዛዥ የሚመደብ ሌላ ኃላፍ ወይም አስጂ በድምጽ ወይም ያለድምጽ የማኔጅመንት አባል ሊያካትት ይችላል፡፡

12. <u>የማኔጅመንት ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>

1) የተቋሙን የበጀት ፍላጎት አጽድቆ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፡፡
2) የትጥቅ ግዥ ፍላጎት ተወያይቶ ያጸድቃል፤
3) የክልሉ ፖሊስ ሠራዊት ዓመታዊ ዕቅድ ላይ ተወያይቶ ያፀድቃል፤
4) በክልሉ የፖሊስ አደረጃጀትና የአገለግሎት አሠጣጥ ደረጃ የፖሊስ አባላት ምልመላ

horaamishsha suusa uynanni gara, wodhote uddano u’dhinanni gara, qodhotenna wole xaaddanno hajubba aana gobbate deerrinni gutu songora kaajjinoha jeefishsha harunsanno;

5) Babbaxitino opireeshiinalete hajubba aana hasaabbe gumultanno; jeefishsha keentanno;

6) Poolisete miillara babbaxitino horaamiishsha xiinxallite kaajishatenni, loosu aana hosiisanno; tittirsha wodhotenni gumulanni;

7) Qoqqowu poolisete wolqa massagantanno seeru jeefishsha keentanno, hasiisannoha ikke leelliro woyyeessate hedo shiqishshanno, biddisa kaajjishanno, jeefishsha harunsitanno;

8) Poolisete miilla rosunna qajeelishu mixo xiinxallote aana xintante kaajishshanno; jeefishsha harunsitanno;

9) Xaphoomu biddishshinna poolisete biddishshubba mereero danchu loosu xaadooshshi heeranno gede injeessitanno;

10) Xaphoomu biddishshi hajajanchi aanno woloota hajubba aana hasaabbanno, gumulo saayisanno;

11) Manaajimentete komite miilla gutunni gumultanno gumulora gutunna hojji yawo noonsa;

12) Manaajimentete gambooshshu yannanna amanyooti biddisunni gumulamanno.

ቅጥር፣ በትምህርትና ስልጠና፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም፣ በማዕረግ አሠጣጥ፣ ደምብ ልብስ አለባበስ፣ ትጥቅና ሌሎች ተዛማች ጉዳዩች ላይ ሀገር አቀፍ ደረጃ በጋራ ጉባኤ የጸደቀውን አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤

5) የተለዩ ኦፕሬሽናል ጉዳዩች ላይ ተወያይቶ ይወስናል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6) ለፖሊስ አባላት የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን አጥንቶ በማፀደቅ፣ ተግባራዊ ያደርጋል ዝርዝሩ በደምብ ይወሰናል፤

7) የክልል ፖሊስ ሠራዊት የሚመራባቸውን ሕግ አፈጻጸም ይገመግማል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤ መመሪያ ያፀድቃል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

8) የፖሊስ አባላት የትምህርትና ሥልጠና ዕቅዶችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል ፣

9) በጠቅላይ መምሪያውና ፖሊስ መምሪያዎች መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ያመቻቻል፤

10) ለጠቅላይ መምሪያ አዛዡ በሚመሩለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሳኔ ያሳልፋል፣

11) የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት በጋራ በሚወስኑት ውሳኔ የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፤

12) የማኔጅመንቱ የስብሰባ ጊዜና ስነ-ስርአት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**13. <u>Bajeette</u>**

Xaphoomu biddishshira bajeette mootimma gaantannosi

**14. <u>Shallagote Taje</u>**

1) Xaphoomu biddishshi wo'manna halaalanya shallagote taje amadanno;
2) Shallagote tajenna woxu ledo xaaddino sanade gidooyidi odiitenninna qara odiitenni buuxantanno.

**<u>GAFA SASE</u>**

**<u>POOLISETE OWAANTE LAINOHUNNI</u>**

**15. <u>Fila Lainohunni</u>**

1) Xaphoomu biddishshi yanna yannatenni fushshanno safaraano garinni poolisimmate ikkadonna fajjaaleessa ikkitino mannoota filara dandaanno;
2) Konni quwi cinaancho quwa (1) worroonnnihu noo gedeenni heerenna tittirshu gashshootu amaale mini fushshanno wodhoninna xaphoomu biddishshi fushshanno biddisinni xawinsanni;
3) Xaphoomu biddishshi poolisimmate wolqa aantetenni umosi yannicha assate assanno harinshora yannitenna piroofeeshinale mannu wolqa heedhannosi gede baxxitino dandoo noonsa wedellqa hanqaffe amaddanno baxxitino loosu harinsho hasiishshu garinni diriirsara dandaanno.

**16. <u>Mannu Wolqa Gashshoote</u>**

1) Poolisete wolqa miilla gashshootu amaale

13. **<u>በጀት</u>**

ለጠቅላይ መምሪያው በጀት በመንግስት ይመደብለታል፡፡

14. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1) ጠቅላይ መምሪያው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2) የህሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነድ በውጥ ኦዲተር ፤በዋና ኦዲተር ይመረምራል፡፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>ስለ ፖሊሳዊ አገልግሎት</u>**

15. **<u>ስለ ምልመላ</u>**

1) ጠቅላይ መምሪያው በየጊዜው በሚያወጣው መመዘኛ መስፈርት መሠረት ለፖሊስነት ብቁ እና ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ሊመለምል ይችላል፤
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝሩ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጠው ደንብ እና በጠቅላይ መምሪያው በሚወጣው መመሪያ ይገለጻል፡፡
3) ጠቅላይ መምሪያው በፖሊሳዊ አቅም በቀጣይ እራሱን ለማዘመን በሚያደርገው ሂደት ዘመናዊ እና ፕሮፌሽናል የሰው ሀይል አቅም እንዲኖረው ልዩ ክህሎት ያላቸው ወጣቶችን አቅፎ የሚይዝ ልዩ አሰራር እንደአስፈላጊነቱ ሊዘረጋ ይችላል፡፡

16. **<u>የሰው ሀይል አስተዳደር</u>**

1) የፖሊስ ሰራዊት አባላትን የክልሉ ምክር

mini fushshanno wodho garinni filanno, qajeelshiishanno, qaxaranno, gashshanno, geegisanno;

2) Qoqqowu poolise miilla qaxaranni yannara dirisi 18 ajinokkihanna 25 diri roorinokkiha ikkanno. Woloota safaraano wodhote gumulanni.
3) Konni quwi cinaancho quwa (1)nna (2) garinni assinanni filatenna qaxarate assooti koo/teemate kiiro amadinoha ikkanno;
4) Qoqqowu poolise loosira hasiisannoha ikke leelliro mootimmate loosaasine lallawininna woloootu seerubba garinni qaxaranno, gashshanno, geegisanno.

**17. Rosonna Qajeelisha**

Ayino filamino poolisichi woy poolisete wolqa miili xintu poolisimmate rosonna qajeelisha a'dhanno, tittirshu jeefishshi wodhotenna biddisunni gumulamanno.

**18. Qaalu Gondooro**

Aye poolisete miili xintu woy poolisete saayinse qajeelisha gudi gedensaanni looso hanafasira albaanni qaalu gondooro eanno. Tittirsha wodhote gumulanni.

**19. Owaante Afira Lainohunni**

Ayino poolisete miili qallawu, gallanni mini, wodhote uddano, ho'dhishu, xagishshunna woloota owaante baatooshiweelo afiranno gede assinanni, tittirsha wodhotenni gumullanni.

ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ያሰናብታል፡፡

2) የክልሉን ፖሊስ አባላት ሲቀጥር ዕድሜ ከ18 ዓመት ያላነሰና ከ25 ዓመት ያልበለጠ ይሆናል፡፡ለሎች መስፈርቶች በደንብ ይወሰናሉ፡፡
3) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት የሚያደርገው ምልመላና ቅጥር የጸታ ስብጥርን ያካተተ ይሆናል፤
4) ለክልሉ ፖሊስ ስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲቪል ሠራተኛ በክልሉ ሲቪል ሠራተኛ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡

**17. ትምህርትና ሥልጠና**

ማንኛውም ምልምል ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሰራዊት አባል መሰረታዊ የፖሊስነት ትምህርት እና ስልጠና ይወስዳል ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ እና መመሪያ ይወሰናል፡፡

**18. ቃለ-መሐላ**

ማንኛውም የፖሊስ አባል መሠረታዊ ወይም የፖሊስ ሳይንስ ስልጠና እንዳጠናቀቀ ሥራ ከመጀመሩ በፊት መሀላ ይፈጽማል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**19. አገልግሎቶችን ስለማግኘት**

ማንኛውም የፖሊስ አባል የቀለብ የመኖሪያ ቤት የደንብ ልብስ፣ የመጓጓዣና የህክምና እና ለሎች አገልግሎት በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**20. Jawaachishsha**

Poolisete miilla wayyabbino mooralenninna seeda owaante qoqqowu poolisete uurrinsha giddo uytanno gede jawaachishate:

1) Xaphoomu biddishshi hajajanchi mitto minu kameela qaraxiweelo halanyunni hidha dandaanno gede qoqqowu mootimma hajo la’annosi federaalete Mootimma loosi mini ledo halante loossanno. Tittirsha wodhotenni gumullanni.
2) Lamala dironna aleenni Owaante uyino woy wommetenni woy babbaxino fayyimmate qarrinni boordetenni geegisamino aye poolisete miili umisi gallanni mini noosikkita buunxe ilamino basera Quchumu gallanni mini base afira dandaanno gede Mootimma irkko assitanno; tittirsha wodhote gumullanni.
3) Aye poolisete miili lamala diro Owaantete gadachosi gude seeru garinni loosu sheematisi uurranno woyte woy gadachote aana here reyote baxxanno woyte owaantete baatooshshe baantannisi;
4) Aye poolisete miili konni quwira cinaancho quwa (1) kayise (3) geeshsha xawinsoonni jawaachishsha mitte hige calla horonsiranno.

**21. Poolisete Miilomitte Uurritanno Korkaatubba**

1) Reyote baxxiro;

**20. ስለ ማበረታቻ**

የፖሊስ አባላት በላቀ ሞራልና ረጅም አገለግሎት በክልሉ ፖሊስ ተቋም እንዲያበረክቱ ለማበረታታት ፤-

1) የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ አንድ የቤት መኪና ከቀረጥ ነጻ በግሉ መግዛት እንዲችል የክልሉ መንግስት ጉዳዩ ከሚመለከተው የፌዴራል መንግስት መ/ቤት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡ዝርዝሩ በደምብ ይወሰናል፤
2) ሰባት አመት እና በላይ ያገለገለ ወይም በጡረታ ወይም በተለያየ የጤና ችግር በቦርድ የተሰናበተ ማንኛውም የፖሊስ አባል የግል መኖሪያ ቤት እንደሌለው ተረጋግጦ በትውልድ ቦታው በከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ማግኝት እንዲችል መንግስት ድጋፍ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3) ማንኛውም የፖሊስ አባል የሰባት ዓመት አገለግሎት ግዴታውን ጨርሶ በህግ መሠረት የስራ ውል ስቋረጥ ወይም ሲሰዋ የአገለግሎት ክፍያ ይከፈለዋል፡፡
4) ማንኛውም የፖሊስ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1)እስከ (3) የተጠቀሰውን ማበረታቻ ከአንድጊዜ በላይ መጠቀም አይችልም፡፡

**21. የፖሊስ ሠራዊት አባልነት ስለቋረጥበት ሁኔታ**

1) ሲሞት፤

2) Miilu owaantete sheemati yanna goofukkinni geegote xa’mo shiqishenna xa’mo a’dhamooshshe afidhuro;
3) Owaante sufate dandisiissanokki jawa xisso woy bisu xe’nne iillitennasi poolisimmate owaantera ikkado ikka hoogasi xigisaanote boordenni buunxiro;
4) Wommetenni fuliro;
5) Madabanya poolisimmate loosi jeefishshi woy massagaanchimmate ikkado ikka hooga woy disipiliinete xe’nnenni loosoho ikkado hoogasi uurrinsha buuxxuro;
6) Jaddotenni qaxxaro shiqeennasi yoote mini gumulonni hunaancho ikke 2 dironna hakkuyia ale usuru qoricha qorchishiishaminoha ikkiro;
7) Usuru qorichi 2 diri woroonni ikkirono hallanyu qorichishiishaminohu poolisete wolqa agure ba’atenni woy woloota tii’etenna mooralete ledo gurchantanno assootubba jeefisino daafira ikkiro;
8) Konni quwira cinaancho quwa (8) worroonnihu heerirono hunaanchu jaddo loosinohu uyinoonisi gadacho jeefisate aana heereikkiro woy mannu lubbo woy jajja gargarate yaatenni ikkiro woy dancha akatoomenni galataminoha ikkironna 10 diri aleenni poolisete miilomitenni Owaante uyinooha ikkiro 2 diri aleenni usuru humuloonnisiha ikkirono usurunni tidhamanno yannara poolisimmate owaante widira higanno gede assinara dandiinanni.

2) አባሉ የአገልግሎት ውል ዘመኑ ሳይጠናቀቅ የስንብት ጥያቄ አቅርቦ ስንብቱ ሲፀድቅ፤
3) አገልግሎት ለመቀጠል የማያስችል ከባድ ህመም ወይም የአካል ጉዳት ደርሶበት ለፖሊስ አገልግሎት ብቁ አለመሆኑ በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ፤
4) በጡረታ ሲገለል፤
5) በመደነኛ የፖሊስነት ሥራ አፈጻጸም ወይም አመራር ብቁ ባለመሆኑ ወይም በዲሲፒሊን ጉድለት ለስራው ብቁ አለመሆኑ በተቋሙ ሲረጋገጥ፤
6) በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ የተባለለ 2 ዓመት ከዚያ በላይ የእስር ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን፤
7) የእስር ቅጣቱ ከ 2 ዓመት በታች ቢሆንም ግለሰቡ የተፈረደበት ሠራዊቱን መከዳት፣ ወይም ሌሎች ለሂሊና እና ለሞራል ተቃራኒ የሆኑ ዲርጊቶች በመፈፀሙ ከሆነ፡፡
8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው ቢኖርም ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ግዳጅ በመፈፀም ላይ እያለ ከሆነ ወይም የሰው ሕይወት ወይም ንብረት ለመከላከል ሲል ከሆነ ወይም በመልካም ሥነ-ምግባሩ ምስጉን የነበረና 10 ዓመት በላይ በፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ያገለገለ ከሆነ ከ 2 ዓመት በላይ እስር የተፈረደበት ቢሆንም ከእስር ሲፈታ ወደ አገልግሎቱ እንዲመለስ ሊደረግ ይችላል፡፡

**22. Fajjo Lainohunni**

Aye poolisete miili fultanno Wodho garinni diru fooliishsho fajjonna addi addi fajjo afiranno.

23. **Womme Fulanni Diro**

1) Poolisete miilla womme fultanno diri konni woroonni noo garinni ikkanno:
   (a) Konistaablete qara saajine geeshsha 50 diro;
   (b) Ka'laanchu inispekiterenni kayise inispekiterete suusi noonsarira 52 diro;

2) Xaphoomu biddishshi loosira hasiisannoha ikke leelliro aye poolisete miili Owaante Qoqqowu poolisete galtinote wodho garinni wommete fullanni diri gedensaanni 5 diro roortinokki yannara seedinsara dandiinanni.

**GAFA SHOOLE**

**SUUSU LOPHO, OWAANTENNA MEEDAYE**

**24. Poolisete Suusa**

1) Polisete miilla suusi konni woroonni nooha ikkanno:

i) Konistaabile,
ii) Kaa'lancho Saajine,
iii) Layinki Saajine,
iv) Saajine,
v) Qara Saajine,
vi) Kaa'laancho Inspekitere,
vii) Layinki Inspekitere,
viii) Inspekitere,

22. **ስለ ፍቃድ**

ማንኛውም የፖሊስ ሰራዊት አባል በሚወጣው ደንብ መሠረት የኣመት እረፍት ፍቃድ እና ልዩ ልዩ ፈቃዶች ያገኛል፡፡

23. **የጡረታ መውጫ ዕድሜ**

1) የፖሊስ አባላት የጡረታ መውጫ ዕድሜ እንደሚከተለው ይሆናል፡-
   (ሀ) ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጅን ማዕረግ ላላቸው 50 ዓመት፤
   (ለ) ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስ ፔክተር ማዕረግ ላላቸው 52 ዓመት፤
   (ሐ) የዋና ኢንስፔክተርና ከዚያ በላይ ማዕረግ ላላቸው 55 ዓመት፡፡

2) ለጠቅላይ መምሪያው ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማኝኛውም ፖሊስ አባል አገልግሎት በክልሉ ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጡረታ መውጫ እድሜ በኃላ 5 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

**ስለማዕረግ እድገት፣ አገልግሎት እና ሜዳይ**

24. **የፖሊስ ማዕረግ**

1) የፖሊስ አባላት ማዕረግ የሚከተሉት ናቸው፤

i) ኮንስታብል፤
ii) ረዳት ሳጅን፤
iii) ምክትል ሳጅን፤
iv) ሳጅን፤
v) ዋና ሳጅን
vi) ረዳት ኢንስፔክተር፤
vii) ምክትል ኢንስፔክተር፤
viii) ኢንስፔክተር፤

ix) Qara Inispekitere,

x) Layinki Komaandere,

xi) Komaandere,

xii) Kaa’laancho Komishiinere,

xiii) Layinki Komishiinere,

xiv) Komishiinere.

2) Konistaabilite qaru saajine geeshsha kaimu massagaano, ka’laanchu inispeekiterenni inispekiterete geeshsha mereerima massagaano, qara inispeekiterenni kayise komaannderete geeshsha aliidi massagaano, ka’laanchu komishiinerichinni kayise komishiinerichu geeshsha isitrateejike massagaano yaamante gaamantanno.

3) Konni quwira cinaancho quwa (1) worroonni poolisete suusira uminsa badooshshu malaati heeranonsa. Tittirshu wodhotenna biddisunni gumulamanno.

4) Konni quwira cinaancho quwa (2) worroonni suusi deerrinni aananno deerri widira reekkamate qoqqowu Poolisete kolleeje qixxeessitanno fonqolo sa’anna qajeelisha guda noosi.

5) Konni quwira cinaancho quwa (2) worroonnihu noo gedeenni heerenna konni quwira cinaancho quwa (1) xawinsoonni suusi keeshshote yanna wodhote gumulanni.

## 25. Suusu Lopho Uynanni Gara

1) Tittirshu jeefishsha wodhote gumulanniha ikke aye poolisete miili lopho hooltanno ikkitubba heera hoogguro suusu keeshshate yanna gudironna

ix) ዋና ኢንስፔክተር፤

x) ምክትል ኮማንደር፤

xi) ኮማንደር፤.

xii) ረዳት ኮሚሽነር፤

xiii) ምክትል ኮሚሽነር፤

xiv) ኮሚሽነር፤

2) ከኮንስታንል እስከ ዋና ሳጂን ጀማሪ አመራር፤ ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር መካከለኛ አመራር፤ ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ኮማንደር ከፍተኛ አመራር፤ ከረዳት ኮሚሽነር እስከ ኮሚሽነር ጀነራል ስትራቴጂክ አመራር ተብለው ይመደባሉ፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (1) ለተመለከቱት የፖሊስ ማዕረጎች የየራሳቸው መለያ ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በአፈጻጸም በደንብ እና መመሪያ ይወሰናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)የተደነገጉት የማዕረግ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመሸጋገር የክልሉ ፖሊስ ኮሌጅ የሚዘጋጀውን ፈተና ማለፍ እና ስልጠናውን ማጠናቀቅ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፀ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የማዕረግ ቆይታ ጊዜ በደምብ ይወሰናል፡፡

## 25. ስለ ማዕረግ እድገት አሰጣጥ

1) ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም የፖሊስ አባል እድገትን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር የማዕረግ ቆይታ ጊዜ ሲያጠናቅቅ እና በሥራ

loosu jeefishisinni duushshanno guma marakesisiro suusu lophpo heewoteninna qajeelishunni afiranno;

2) Konni quwira cinaancho quwa (1) garinni suusu lopho uynanni yannara koo/teemate amado hedote giddora eessa hasiisanno;

**26. Wole Mootimmate Loosi Minira Assinanni Basete Soorro**

1) Mootimma hasiissannota ikkite leelturo mitto poolisete miila wolu mootimmate loosi minira woy latishshu uurrinsha widira sufametenni woy yannate geeshshira dargu soorro assite loosiisa dandiitanno;
2) Qoqqowu poolise xaphoomu biddishshi hasiisannoha ikke leellisironna haaranno loosi mini hattono dargu soorro assano poolisete miili sumuu yituro mitto poolisete miila wolu mootimmate loosi minira woy mootimmate latishshu uurrinsha widira uurrinshatenni dargu soorro assa dandiinanni.
3) Konni quwira cinaancho quwa (1)nna (2) worroonnihu garinni sooramino miili qoososinna gadachosi soorrote harino loosi mini galanno seerinni galannoha ikkanno.

**27. Poolisete Baraarshi Dana, meedaye, Woyyaawino Loosi Riivane, Woxenna Tajete Woraqata**

Woyyaawino gadachote jeefishshi, luphi yiino loosu gumi woy seeda poolisimmate Owaante

አፈፃፀሙ አጥጋቢ ውጤት ሲያስመዘግብ የማዕረግ እድገት በውድድርና በስልጠና ያገኛል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የማዕረግ እድገት ሲሰጥ የዖታ ተዋጽኦ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

**26. ወደ ሌላ የመንግስት መ/ቤት የሚደረግ ዝውውር**

1) መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የፖሊስ አባል ወዳ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጀት በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ አዛውሮ ማሰራት ይችላል፤
2) ክልሉ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አሰፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና የተቀባይ መስሪ ቤት እንዲሁም የሚዛወረው የፖሊስ አባል ሲስማሙ አንድን የፖሊስ አባል ወደ ሌላ የመግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድረጅት በቋሚነት ማዛወር ይችላል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው መሠረት የተዛወረ አባል መብቱንና ግዴታው የተዘወረበት መስሪያ ቤት በሚተዳደርበት ህግ የሚገዛ ይሆናል፡፡

**27. የፖሊስ የሽልማት አይነቶች ሜዳዮች የላቀ ሥራ ሪቫይን ገንዘብና የምስክር ወረቀት**

በላቀ የግዳጅ አፈጻጸም፣ በላቀ የሥራ ውጤት ወይም ረጅም የፖሊስ አገልግሎት ላበረከተ የፖሊስ አባል የሚሰጥ የጀግንነት ሜዳይ፣ የላቀ

uyino poolisete miilira uynanni bareendete meedaye, liphi yiino loosu gumi meedaye, owaantete meedayenna riivane woxu ledo uynanni tajete woraqati heeranno; tittirsha wodhote gumulanni.

**<u>Gafa Onte</u>**

**<u>Gutu Songo Uurrisanna Gashshootu Taqqara Afantanno Woshshamaano Uurrinshuwa Ledo Hee’ranno Xaadooshshe</u>**

**28. <u>Qoqqowu Poolisete Xaphoomu Biddishshinna Poolosete Biddishshi Gutu Songo Uurrisate Daafira</u>**

1) Xaphoomu biddishshinna Zone hattonni Zonete deerrinni noo Quchumu gashshooti biddishshira heedhannonsa tantano agarantino gede heedheenna mereeronsa hee’ranno xaadooshshe kajjishate dandiisiissannoti gutu songo Konni ka’a gutu songo yine woshshinanniti konni lallawinni Uurritino.
2) Songote Miilla:
   (a) Xaphoomu Poolisete Biddishshi hajajanchi…………Gambiisaancho;
   (b) Laayinki Xaphoomu Biddishshi hajajaano, Zoonetenna Hawaasi Quchumu Gashshooti poolisete Biddishshi Hajajaano…………………………Miilla;
   (c) Xaphoomu Poolisete Biddishshi hajajanchi hasiisanno garinni huuriweello woloota hajo xawisate beeqqitannore poolisete miilla leda dandaanno.
   (d) Xaphoomu Poolisete Biddishshi hajajanchi borro mini sooreessi borreessaancho ikkanno.

ሥራ ውጤት ሜዳይ፤ የአገለግሎት ሜዳይ እና ሪቫን ከገንዘብ ጋር የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ይኖራሉ፤ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>የጋራ ጉባኤ መቋቋም እና በየአስተዳደር እርከኑ</u>**

**<u>ከሚገኙ ተጠሪ ተቋማት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት</u>**

**28. <u>የክልል ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ እና የፖሊስ መምሪያ የጋራ ጉባኤ ስለማቋቋም</u>**

1) ጠቅላይ መምሪያው እና የዞን እና በዞን ደረጃ ያለ ከተማ አስተዳደር መምሪያ የሚኖራቸው አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል የጋራ ጉባኤ ከዚህ በኃላ ጉባዔው እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2) የጉባኤው አባላት

(ሀ) የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ…..ሰብሳቢ፤

(ለ) የምክትል ጠቅላይ መምሪያ አዛገሮች፣ የዞን የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ አዛገሮች አባል፤

(ሐ) የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ እንደ አስፈላጊነቱ ያለ ድምጽ በአስረጅነት የሚሳተፉ ሌሎች የፖሊስ አባላት ሊያካትት ይችላል፡፡

(መ) የጠቅላይ መምሪያው አዛዥ ጽ/ቤት ኃላፍ ፀሐፊ ይሆናል፡፡

29. **Gutu Songo Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1) Qoqqowoho poolisete ogimmanna Akatoominni subbinonna Tekinoloojjetenni irkisante yannissino Poolisete Uurrinshsha qoqqowoho, zoonnatenna Hawaasi quchumi gashshootira ijaartanno gara qinneessitanno;
2) Poolisete wolqa miilla filo,Qajeelsha, Gaamooshshenna Gashshootu hajubbanna wole horo lainohunni Gobboomu safaraanchi assooti hee'ranno gede assitanno;
3) Qoqqowu Xaphoomu Biddishshubbara heedhaara hasiissanno Tantanonna qodho lainohunni Fultinota Poolisete Istaandaarde xintinni ikkase Keentanno, Harunsitanno, Qorqortanno;
4) Jaddonna Jaddote yaaddo ajishate hayyo injeessitanno, Jaddo gargarate loosira dagate beeqqo kaajjishate Dagoomu beeqqo poolisete owaante loosu aana hosase buuxxanno, Gumulsha ha'runsitanno, Taashshate qaafo adhitanno;
5) Qoqqowu Poolisete wolqa Xaphoomu Biddishshi Zoonenna Quchumu gashshooti biddishshuwa waaxante irkisamatenninna poolisete wolqa ariggiratenni loossanno gara qineessitanno;
6) Sidaamu Dagoomi Qoqqowi poolise

29. የጋራ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባራት

1) በክልሉ በፖሊሳዊ ሙያና ሥነ-ምግባር የታነፁ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የፖሊስ ተቋም በክልል፣ በዞኖች እና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የሚገነባበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
2) የፖሊስ ሰራዊት አባላት ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ቅጥርና አስተዳደር ጉዳዮችና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ ሀገር አቀፍ ወጥነት ያለው አሠራር እንዲኖር ያደርጋል፣
3) በጠቅላይ መምሪያ ሊኖር የሚገባውን አደረጃጀት እና ትጥቅ በተመለከተ በወጣው የፖሊስ ስታንዳርድ መሰረት ስለመሆኑ ይገመግማል፣ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
4) የወንጀል ስጋትንና የወንጀል ድርጊትን ለመቀነስ የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ወንጀል በመከላከል ተግባር ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ለማጠናከር የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ተግባራዊ ስለመደረጉ ያረጋግጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
5) በክልል ፖሊስ ሰራዊት ጠቅላይ መምሪያው እና በዞኖችና ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች በቅንጅት በመደጋገፍ እና የፖሊስ ሀይል በመዋዋስ የሚሰሩበት ሁኔታ ያመቻቻል፣
6) የሲዳማ ብሄራዊ ክልል ፖሊስ ከአጎራባች

Qooxeessu qoqqowubba ledo mashalaqqete soorrishshi amuraate diriirsatenni kajjishshanno ikkito qineessitannao faashsho wortanno.

7) Gobboomu deerrinni Diru dirunni Wo'manka wooyte Arfaassa 23 ayirrinsanni poolisete wolqa barri ayyaani ayirrishshi amuraate qixxessitanno, Massagganno, Gumulsiissanno.
8) Poolisete wolqa miillata uurrinshshaame laonna mittimma kaajjishate Qoqqowu deerri poolisete wolqa ispoortete heewo ha'rnsanni gede assitanno.
9) Poolisete miilla jawaachishate gallanni mine loosate uynanni kaa'lo loosu aana hossanno gede mitteenni loossanno;
10) Songotenni uynoonni gumulo baalante poolisete wolqa uurrinshshuwara loosu aana hosase keentanno, Laanfete aana faashsho wortanno, Hajo la'anno mootimmate bisira shiqishshanno;
11) Qoqqowu Poolisete wolqa loosu mixo balaxxe haa'dhanno, Keentanno loosu aana hosase harunsitanno;
12) Jaddo gargaratenna Qorto buuxate fooreeme qoqqowu deerrinni uurrissanno Jeeifishshiserano mittimmatenni loossanno;
13) Gutu songo harinsanni Zoone woy Quchumu gashshoote gumultanno.

ክልል ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የሚዘረጋበትና የሚጠናከርበት ሁኔታ ያመቻቻል አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

7) በየአመቱ ጥር 23 ቀን የሚከበረውን ብሄራዊ የፖሊስ ሰራዊት ቀን በዓል አከባበር አጀንዳ ይቀርጻል፣ ይመራል ፣ያስፈጽማል፣
8) የፖሊስ ሰራዊት አባላትን ተቋማዊ አመለካከትና አንድነት ለማጠናከር ክልላዊ የፖሊስ ሰራዊት የስፖርት ውድድሮች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡
9) ለፖሊስ አባላት የሚሠጠው የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ማበረታቻ ተግባራዊ እንዲሆን በጋራ ይሠራል፡፡
10) በጉባኤው የተወሰኑ ውሳኔዎች በሁሉም የፖሊስ ሰራዊት ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይገመግማል ፣ በክፍተቶቹ ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ለሚመለከተው የመንግስት አካልም ያቀርባል፣
11) የክልሉን የፖሊስ ሰራዊት የሥራ እቅድ አስቀድሞ ይቀበላል፣ ይገመግማል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
12) የወንጀል መከላከልና ምርመራ ፎረሞችን ክልል አቀፍ ደረጃ ያቋቁማሉ ለተግባራዊነቱን በጋራ ይሠራል፡፡
13) የጋራ ጉባዔው የሚካሄድበትን ዞን ወይም ከተማ ይወስናል፡፡

**30. Gutu Songo Gambooshshe**

1) Gutu songo dirunni 2 hige madabanya gambooshshe harissanno, ikkeenano hasiishshu garinni winaamu gambooshshe assitara dandiitanno;
2) 2/3kki ikkitanno gutu songo miilla gambooshshu aana leelturo wo'ma songo ikkitinohu gede kiiranni;
3) Gutu songo gumulo huurote roorrenni gumulantanno, ikkeenano huuro taalo dagguro gambisaanchu noo ragi songote gumulo ikkanno;
4) Gutu songora umise gambooshshu amanyooti biddisa fushshidhara dandiitanno.

**31. Gashshootu Taqqara Afantanno Hundaasine Poolisete Biddishshubba Ledo Heerano Xaadooshshu Amuraate**

Deerra deerraho noo gashshootu taqqara afantano hundaasine poolisete Biddishubba:

1) 24 sa'atenna 15 barrinni jaddote ga'labbo mashalaqqe rippoorte sayisanno;
2) Jaddotenna Wodho sa'ate isitastikise mashalaqqe aganunni, sasu aganinni, lewu aganinni, honsu aganinninnadirunni rippoorte assitanno;
3) Olu bagado qodho tantano lainohunni Qoqqowu poolise hunda tantanantanno

**30. የጋራ ጉባኤው ስብሰባ**

1) የጋራ ጉባዔው በዓመት(2) ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2) 2/3ኛ የሚሆኑት የጋራ ጉባዔው አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
3) የጋራ ጉባዔው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይወሰናሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4) የጋራ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**31. በየአስተዳዳር እርከኑ ከሚገኝ ተጠሪ ፖሊስ መምሪያዎች ጋር ስለሚኖር የግኑኝነት ሥርዓት**

በየአስተዳዳር እርከኑ ከሚገኝ ተጠሪ ፖሊስ መምሪያዎች፤

1) የ24 ሰዓት እና የ15 ቀኑ የወንጀል ጸጥታ መረጃ ሪፖርት ያስተላልፋሉ፤
2) የወንጀል እና የደምብ መተላለፍ ስታቲክስ መረጃ በወር፣በሶስት ወር በስድስ ወር በዘጠኝ ወር እና በዓመት ሪፖርት ያደርጋሉ፤
3) የጦር መሳሪያ ትጥቅ አደረጃጀት በተመለከተ በክልል ፖሊስ በሚደራጀው ሀገር አቀፍ የጦር መሳሪያ የመረጃ ቋት

gobbate deerri olu bagado mashalaqqete shae giddo lewu aganinni rippoorte assitanno;

4) Poolisete miilla batinyenna halanyu mashalaqqe xaphoomu biddishshira lewu aganinni rippoorte assitanno; gobbate deerrinni mashalaqqete shae giddo mashalaqe noosikki poolisete miili aye Owaante afira didandaanno;
5) Xaphi yitino poolisete diru mixo, lewu aganinna diru jeefishshi rippoorte shiqishshanno.

**32. <u>Federaalete Poolisenna Wolootu Qoqqowubba Poolise Xaphoomu biddishubba Ledo Heeranno Xaadoshshe Lainohunni</u>**

1) Xaphoomu biddishshi jawanna gashshootu danna sa’anno jaddo qinaawino garinni gargaratenna buuxate injo kalaqanno;
2) Rakkino data beeze diriirsatenni yannite mashalaqqe federaalete poolisete uurrinsharanna miilla ikkitino qoqqowubbara beehatenni jaddo gargaronno, buuxanno;
3) Dhuka dhaabachiishate qajeelishinni mannu wolqa lossatenna gobbate deerinni deerrase agadhitinota ikkitanno gede dandiisisate assinanni lamunnu hakuyi ali ka’lamooshshe assanno.

ውስጥ በየ6 ወሩ ሪፖርት ያደርጋሉ፤

4) የፖሊስ አባላት ብዛትና የግል መረጃ ለጠቅላይ መምሪያው በ6(ስድስት) ወሩ ሪፖርት ያደረጋሉ፤ በሀገር ደረጃ የመረጃ ቋት ውስጥ መረጃ የሌለው የፖሊስ አባል ማንኛውም አገለግሎት ማግኘት አይችልም፡፡
5) ጥቅል የፖሊስ ዓመታዊ ዕቅድ የስድስት ወር እና የዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባሉ

**32. <u>ከፌዴራል ፖሊስ እና ከሌሎች ክልሎች ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>**

1) ጠቅላይ መምሪያው ከባድና ወሰን ተሻጋሪ የሆኑ ወንጀሎች በተቀናጀ ሁኔታ ለመከላከልና ለመመርመር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
2) ፈጣን ዳታ ቤዝ በመዘርጋት ዘመናዊና ወቅታዊ መረጃ ለፌዴራል ፖሊስ ተቋም አባል ክልሎች በማካፈል ወንጀልን ይከላከላል፤ ይመረምራል፡፡
3) በአቅም ግምባታ ስልጠና የሰው ኃይል ለማብቃትና አገር አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የሚደረጉ የሁለትዮሽ እና ከዛ በላይ ትብብሮች ያደርጋል፡፡

## GAFA LEE

## ADDI ADDI WORO

**33. Hirotenna Jajju Gashshoote**

Xaphoomu biddishshi hirotenna jajju gashshooti mootimmate hirotenna jajju gashshooti lallawininna lallawa harunsite fultanno biddisubba garinni jeefamanno.

**34. Lekkishsha Aa Lainohunni**

1) Xaphoomu biddishshi baxxitino ogimma xa’mitanno hajubbara garimma noonsa wolootu seerubbanni galanno aye manchira biilloonyisi aaninni bocunni woy wo’munni wo’ma lekkishunni aara dandaanno.
2) Konni quwi cinaancho quwa (1) woro garinni uynanni lekkishshi hajote hasiisanno bikini calla ikkanno.

**35. Halamate Gadacho**

1) Xaphoomu biddishshi konni lallawira worroonni jaddo gargaratenna qorto buuxate ledo xaaddanno loossa loosanno woyte hajo la’annosari baalu halamate gadacho noonsa;
2) Konni quwira cinaancho quwa (1) garinni gadachosi fulinokki manchi konni lallawininna garimma noonsa wolootu seerubbanni xa’mamannoha ikkanno.

**36. Hoolloonnire**

Poolisete loossa jeefisate ragaanni konni

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**33. ግዥና ንብረት አስተዳደር**

ጠቅላይ መምሪያው ግዥና ንብረት አስተዳደር በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ይፈጸማል፡፡

**34. ውክልና ስለመስጠት**

1) ጠቅላይ መምሪያው ልዩ ሙያ ለሚጠይቁ ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች ለሚተዳደር ማንኛውም ሰው ከስልጣኑ በከፍል ወይም በሙሉ በውክልና ሊሰጥ ችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚሰጥ ውክልና ለጉዳዩ አስፈላጊ በሆነው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

**35. የመተባበር ግዴታ**

1) ጠቅላይ መምሪያው በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ከወንጀል መከላከልና ምርመራ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ሲወጣ የሚመለከታቸው ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ሰው በዚህ አዋጅና አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች ተጠያቂ ይሆናል

**36. ክልከላዎች**

የፖሊስ ተግባርትን በመፈጸም ረገድ ከዚህ በታች

woroonni noore hoolloonni:

1) Manhiimate gobbaanni woy ayirinye kisanno amadooshshe woy assote jeefisa;
2) Gosoomitetenni, dagoomitetenni, qalamtenni, koo/teematenni, afuunni, ammanotenni, poletiku la'ooshshinninna dagoomitete kaiminni, jirote, ilamate woy wolu aye korkaatinni badooshshe kalaqa;
3) Aye poolisete miili woy siviile loosaasinchi poletiku biilloonyi doorshu heewora beeqqate hasirannoha ikkiro balaxe loososi agura noosi;
4) Konni quwira cinaancho quwa (4) worroonnihu noo gedeenni heerenna doorshunni qeeliro woy qeelamiro hige uurrinshate looso sufa didandaanno.

37. **<u>Jaddote Xa'mamooshshe</u>**

Konni lallawira worroonni halamate gadachonna hoolloonnire ayirisanokkihu, baxxino garinni fajja hoongiro Sidaamu dagoomi Qoqqowu Mootimma wodhote uddano latisinohu, hidhinohu, uddirinohu, duuninohu woy sayikki bisira sayise uuyinohu woy poolisete ayimmate kaarde seeru gobbaanni amadinohu, horonsirinohu, poolisete ayirinyenna dancha su'ma xursanno addi addi assoote loosinohu aye manchi jaddote seerinni woy wolootu garimma noonsa seerubba aana

ያሉትን መፈጸም የተከለከለ ነው፤

1) ኢ-ሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት መፈፀም
2) በዘር፣ በብሄር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖሊቲካ አመለካከት እና በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት በትውልድ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
3) ማንኛውም የፖሊስ አባል ወይም ሲቪል ሠራተኛ ለፖሊቲካ ስልጣን ምርጫ ውድድር ለመሳተፍ የሚፈልግ ከሆነ በቅድሚያ ሥራውን መልቀቅ አለበት፡፡
4) በዚህ አንፅ ንዑስ አንቀጽ(3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫው ቢያሸንፍ ወይም ቢሸነፍ ተመልሶ በተቋሙ ሊቀጥል አይችልም፡፡

37. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

በዚህ አዋጅ የመተባበር ግዴታ እና ክልከላዎችን **የማያከብር**፣ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ፖሊስ የደንብ ልብስ ያመረተ፣ የገዛ፣ የለበሰ፣ ያከማቸ፣ ወይም ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ ወይም የፖሊስ መታዊያ ያለህጋዊ ምክንያት የያዘ፣ የተገለገለ፣ የፖሊስን ክብርና መልካም ስም የሚያጎድፉ የተለያዩ ድርጊቶች የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ህጉ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ላይ የተቀመጠው ቅጣት ተፈጻሚ

worroonni qorichi jeefamannosi.

**38. Wodhonna Biddisa Fushshate Biilloonye**

1) Jefisiisanote amaale mini konne lallawa loosu aana hosiisate Wodho fushshanno.
2) Sidaamu dagoomi Qoqqowu Mootimma xaphoomu biddishshi konne lallawanna konne lallawa loosu aana hosiisate fultanno Wodho jeefisiisate biddisa fushshanno.

**39. Reekkote Woro**

1) Konni lallawi ledo kiphama hoogiro Poolisete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawi Kiiro 7/2013 garinni seeru garinni hanfantinonna kuni lallawi loosu aana hosasira albaanni jeefantinokki aye qoosso, gadacho, sheemati, qorto, gashshootu harinsho woy jefisiisate qaafo kaajjite keeshshitannohanna suffannoha ikkanna gumulo afidhannohu albi lallawira worroonnihu garinni ikkanno.
2) Poolisete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawi Kiiro 7/2013 garinni poolisete komishiinera uynoonni biilloonyinna loosu qeechi, qoosso, asali, jiro, tajenna gadacho wo'munni wo'ma kuni lallawi kaajje loosu aana hosi gedensaanni konni lallawinni marro tantanamino Sidaamu Qoqqowu Xaphoomu Biddishshira sa'inno.
3) Xaphoomu biddishshi kuni lallawi loosu aana hosi yannanni hanafe 6 agani giddo wo'munni wo'ma Baatto kadisiisate baalanta hasiissanno gashshootamenna seeru qaafo a'dhanno.

ይሆንበታል፡፡

**38. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ያወጣል፡፡
2) ጠቅላይ መምሪያው ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ስራ ላይ ለማዋል የሚወጣውን ደንብን ለማስፈፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

**39. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1) ከዚህ አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ የፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/2012 መሠረት በህጋዊ መንገድ የተጀመረ እና ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ያልተፈፀመ ማንኛውም መብት፣ ግዴታ፣ ውል፣ ምርመራ፣ አስተዳደራዊ ሂደት ወይም የማስፈጸሚያ እርምጃ ፀንቶ የሚቆይ እና የሚቀጥል እና የሚጠናቀቀው በተሻረው አዋጅ በተደነገገው መሰረት ነው፤
2) በአዋጅ ቁጥር 7/2012 መሰረት ለፖሊስ ኮሚሽኑ የተሰጠ ሥልጣን፣ ተግባር፣ መብት፣ ዕዳ፣ ሀብት፣ መዝገቦች እና ግዴታዎች በሙሉ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በዚህ አዋጅ እንደገና በተደራጀው ለሲዳማ ክልል ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ተላልፈዋል፤
3) ጠቅላይ መምሪያው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለ በስድስት (6) ወራት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉንም አስፈላጊ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

40. **Jeefishshu Noonsakki Seerubba**

1) Sidaamu Dagoomi Qoqqowi Mootimma Poolisete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawi Kiiro 7/2013 konni lallawinni shaaramino.
2) Konni lallawi ledo kiphamanno aye lallawi, Wodho, biddisi, rosamino assooti konni lallawi giddo diwantino hajo aana jeefishshu diheeranoonsa.
3) Konni quwira cinaancho quwa (1)nna (2) worroonnihu noo gedeenni heerenna Poolisete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawi Kiiro 7/2013 garinni fultino aye Wodho, biddisi, gumulo woy qaafo konni lallawi ledo kiphantanokkiha ikkiro konni lallawi garinni fultanno wodhoninna biddisinni riqiwantano woy shaarantanno geeshsha loosu aana keeshshitanno.

41. **Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna**

Kuni lallawi Qoqqowu Amaale Mininni kaaji …..barinni 2017 M.D hanafe loosu aana hosanna.

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma Prezidante**

40. **የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1) የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት የፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/2012 በዚህ አዋጅ ተሽሮዋል፡፡
2) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/2012 መሠረት የወጣ ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ፣ ውሳኔ ወይም እርምጃ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣረስ እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እስኪተካ ወይም እስኪሻር ድረስ ጸንቶ ይቆያል።

41. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት …… ቀን 2017 ዓ፣ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ፕሬዝዳንት**